# ይውጋሽ ብሎ ይማርሽ ፤ አዲስ ፖለቲካ

ከአይምሮ ዳኛቸው

በቅርቡ ወደ ስድስት የሚጠጉ የፖለቲካና የሲቪክ ማህበሮች በአንድነት በመሆን የጋራ መግለጫ ማውጣታቸው ይታወቃል ። በአጭሩ ይህ መግለጫ ከዚህ ቀደም እንደ ክፉ ተላላፊ በሽታ በሩቁ ሲሸሹትና ሲርቁት የነበረውን ድርጅትና የፖለቲካ እስረኞቻቸውን የሥም ዝርዝር ከአዳዲሶቹ የፖለቲካ እስረኞች ጋር በማከል ከወትሮ የአሰራር ዘይቤያቸው የተለየ እንደሆነ አድርጎ ሊያሳይ ሞክሯል ። የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን የኢሕአፓ ታጋዮችን ሥም እንደ ጸጋዬ ገ/መድህን (ደብተራው) አበራሽ በርታና የመሳሰሉትን ሥሞች በመጥቀስ ከእስርም እንዲፈቱ በመጠየቅ ያደረጉትን ጥሪ ስመለከት እውነትም እነዚህ ቡድኖች አሁን ወደ ህሊናቸው እየተመለሱ ነው ፤ አይናቸውም አይምሯቸውም ተገልጧል ፡ አሁን በቁርጠኝነት ወያኔን ሊታገሉ ተነስተዋል በማለት እጅግ በጣም ደስ አለኝ ።

ሆኖም ግን አንድ ምዕራፍ ወደ ታች ወረድ እንዳልኩ ደስታዬ ወዲያውኑ ጨለመ ፤ ልቤ ክፉኛ በሀዘን ተመታ ፤ የቀድሞ የተለማማጭነት ባህሪያቸው እንዳልተለወጠ አብሯቸው እስከ መቃብር እንደሚጓዝ በማያሻማ አማርኛ አስቀምጠው ዛሬም ወያኔን ደጅ እየጠኑ መሆናቸውን ሳይፍሩ አስታወቁ ። አስቀድመው ያስቀመጡት ግር ግር ሁሉ የውሃ ሽታ ሆነ ለካስ ጨዋታው አልሸሹም ዞር አሉ ኖሯል ።

ያሰፈሩት ጽሁፍ ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል :-

<u>“ሀገራችን አንድነቷና ሉአላዊነቷ ተከብሮ፣ ሰላምና ፀጥታዋ ተጠብቆ፣ ህዝቧ በነፃነትና በእኩልነት የመኖርና የመሥራት መብት ተከብሮለት፣ የበለፀገች እንድትሆን፣ ገዥው ፓርቲ፣ የፖለቲካ ምህዳሩን ክፍት እንዲያደርግ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።”</u> ይላል::

እኔ ይህን አባባል በቀጥታ እንደገባኝ ሲተረጎም ፤ የሚለው “አባታችን ወያኔ ሆይ ፤ ባራት ኪሎ የምትኖር ፤ ሥልጣንህ ትርጋ ፤ የድርሻችንንም አትንሳን ፤ ለምኑ ታገኛላችሁ ፤ አንኳኩ ይከፈትላችኋል ባልከው መሰረት ፤ ከበርህ ቆመን ደጅ እንጠናለንና ፈቃድህ ይሁን ነው የሚለው፤ ይህ አባባል ወደ ግራም ይሁን ወደ ቀኝ ብናገላብጠው እባክህ መልካም ፈቃድህ ሆኖ መጪውን ምርጫ እንድንካፈል ፍቀድልን ከማለት በቀር ሌላ ቁም ነገር የለውም ።

ይሄ እየሸሹ መታገል ፤ እየታገሉ መሸሽ የሚለው መርኋቸው ሊገባኝ አልቻለም ፤ ይሄንን ስብስብ በበላይነት ወደ ግራና ቀኝ የሚያወዛውዙት ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ወያኔን ጠላት ነው ብለው መፈረጅ ያልቻሉ ፤ ልባቸው መቁረጥ አቅቶት አንዴ ወደግራ ፤ አንዴ ወደቀኝ ሲዋዥቅና ሲዋልል የሚኖር መሆኑን በተደጋጋሚ አስመስክረዋል ። እራሳቸው የሚናገሩትን ካለማወቃቸው የተነሳ ተወናብደው

ሊያወናብዱ ሲሞክሩ እውነት አራዳነት ማለት ይህ ከሆነ የፋራው ፍልስፍና ምንኛ እንዳስከነዳቸው ነጋሪም ባላሻቸው ነበር ።

ካገር ቤት እየፈረጠጡ ወጥተው ዲያስፖራ ሲደርሱ ደርሶ ጀግና መምሰል አልገባኝም ፤ ያም ይሁን እንኳን ቢባል አገር ቤት በድፍረት ተጋፍጦ እየተዋጋ ያለውን እናግልል ገለመሌ እያሉ ያልሆኑትን መሆን ምን ይባላል? ከየትስ የመጣ ነው? ሁሌም በሽሽትና ከትግል ሜዳ ፈርጥጦ በመጥፋት ታዋቂ የሆኑ ዛሬ ትግል እንምራ ሲሉ ጉዳዩ ከማሳቅም በላይ እየሆነ ነው ፤ ለመሆኑ እየሸሹ መታገል እየታገሉ መሸሽ የኳሊዮሽ ተኩስ ከየት የመጣ የማናውቅው የትግል ዘይቤ ነው ሊያስተምሩን የሚሹት?

እንግዲህ እነዚህ የሚናገሩትን የማያውቁ ወያኔን ጠላት ብሎ መጋፈጥ የተሳናቸው ሆኖም ግን ወያኔን ልንወጋ ጦር እየሰበቅን ነው የሚሉን ታዲያ በነሱ ቋንቋ ወያኔ ጠላት ካልሆነ ጦር የሚሰበቅበት ለምን ይሆን? ወይንስ የነሱ መጸሐፍ ጦር መታወጅ ያለበት በወዳጅ ላይ ነው የሚለው? ወይንስ የወዳጅና የጠላት ትርጉሙ አልገባቸው ብሷል? እንደነሱ አባባል ጦር ማንሳት ያለብን በወዳጃችን እንጂ በጠላታችን ላይ መሆን አይኖርበትም ማለት ነው ፤ አሊያ እነሱ ቤት የወዳጅና የጠላት ትርጉሙ  ቅጥ አንባሩ ጠፍቶት እውር ድንብሩን የሚጋልብ ትርጉም አልባ እንቆቅልሽ ነው ማለት ነው ።

ይህም የሚወራለት ጦራቸው የሚመራው በኮማንደር ኢሳያስ አፈወርቂ ሲሆን የጋንታ መሪዎቹ ደግሞ ዶ/ር ብርሃሁ ነጋና አንዳርጋቸው ጽጌ ናቸው ፤ የሚገርመው ዶ/ር ብርሃኑ በአንድ ወቅት የትጥቅ ትግል ተቃዋሚ ብቻ ሳይሆኑ የትጥቅ ትግል ደጋፊዎችን ጠመንጃ ነካሾች ብለው ይጠሩ የነበረና  እንዲያውም ለማጣጣል ሲሉ  የገበሬውንና የደሃውን ልጅ ለማስጨረስ ነው ብለው የሚወነጅሉ ግለሰብ እንደነበሩ ይታወቃል ፤ ታዲያ ዛሬ እሳቸው ያዘመቱት የሚኒስተሩንና የጀንራሎቹን ልጆች ነው ? ወይስ የቀድሞው ቃላቸውን መልሰው ዋጡት? ትግሉንስ ሲመሩ እንደ ኮማንደራቸው ኢሳያስ አፈወርቂ ወይንም እንደሚወጉት ወያኔው መልስ ዜናዊ በሰራዊቱ መሃል በመሆን ሞቱን እየሞቱ ፤ ቁስሉን እየቆሰሉ ፤ እርሀቡን እየተራቡ ፤ ጥማቱን እየተጠሙ ሊያታግሉ ነው ? ወይስ በምቾትና በድሎት በአውሮፓና አሜሪካ ተቀምጠው ቀጭን ትእዛዝ በመስጠት ነው ድራማውን የሚሰሩት? መልሱን ለባለጉዳዩ እተወዋለሁ ።

አሁን እያስፈራኝ የመጣው ምናልባት ሳናውቀው እንደ ቀድሞ ባቢሎናውያን ከልባችን ክፉት የተነሳ ቋንቋችን ተቀያይሮ ይሆን መግባባት የተሳነን? እያልኩ ለመጠየቅ ተገድጃለሁ ፤ እኛ መወጋት ያለበት ጠላት ነው ስንል በእነሱ ቋንቋ መወጋት ያለበት ወዳጅ ሆኖ ይገኛል ፤ እኛ ትግሉ አገር ቤት ነው ስንል እነሱ ዲያስፖራ ላይ በየ ኢንባሲው ደጃፍ አውጥሃኒ እያሉ ሲያንዛርጡ ይስተዋላል ፤ ታዲያ በዚህ ይዞታና አካሄድ የወረቀት መድፍ ፤ የብዕር ጦር አንግበው አገር ቤት ያለውን ታጋይ እያናናቁ ፤ በዲያስፖራው ድልን አስመዘገብን እያሉ ሲወሸክቱ ይደመጣሉ ። መቼም በዕብዶች ከተማ አንድ ጤነኛ ቢገኝ እሱም ከእብድ ይቆጠራል እንዲሉ እነሱን ያልመሰለውን ሁሉ ዛሬ እንደ ደሃ አጥር ካውገረገሩት ሕብረት ተብዬ ኢትዮጵያዊ ታጋይ ድርጅቶች እንዲገለሉ ሲሉ የትላንቱ አንጃ ተደምጠዋል። ጴጥሮስ እንኳን ጌታን ዶሮ ሳይጮህ ሶስቴ ቢክዳም ነገር ግን በሌላ ክብረ ነክ እዳ ተጠያቂ አልነበረም ፤ የዘመናችን ጴጥሮስ የሆኑት ዶ/ር ጌታቸው ግን ዶሮ ሳይጮህ ሶትና አራቴ መክዳቱ ብቻ ሳይሆን ያደሩበትን ሆቴል ሂሳብ ሳይከፍሉ በጠፍ ጨረቃ የከዱና የኮበለሉ ዛሬ እሳቸውም

መበተንንም ትግል አርገውት እውነተኛ ታጋዮችን መገለል አለባቸው ሲሉ መስማት ለዘመኑ ቲያትር ውበት ሳይሰጠው እንዳልቀረ እገምታለሁ ። በተለይ እንደሳቸው ያለ የትግል ታሪኬ ብለው የሚኮሩብት የትግል ምዕራፍ የሌላቸው ካፋቸው ቆጠብ ቢሉ እኛም ስለሳቸው መፃፍ ባልተገደድን ነበር ። ለነገሩ ሁሎችም አንድ አይንት ባህሪይና ጸባይ ያላቸው ስለሆኑ እዚያው እርስ በርሳቸው ሽታዬ ሽታዬ ይባባሉ እንጂ የሚያውቅ ያውቃቸቃል።

እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማያልፈው የጥርቅሞቹ ሁኔታና ይዘት ነው ፤ በተለይ እራሱን ህብረት ብሎ የሚጠራው እነ ዶ/ር ነገደን ያሰባሰበውና ከቤዝመንት ሆኖ በሚካሄድ ድረ ገጽ ላይ ብቻ የሚታወቀው እንደ ጋሻ ያሉ ቁጥራቸው እጅግ ቢበዛ ከሶስትና ከአራት የማይበልጡ ግለሰቦችን ያካተተ ግሩፕ በፖለቲካ ፓርቲነት ሲቀርብ እውነትም እንዴት መሳቂያዎች ሆነናል የሚያሰኝ ነው ፤ እኔ ደርግ ከስልጣን ከተወገደ ጊዜ ጀምሮ እራሱን በመኢሶን ስም የሚጠራ ፤ መኢሶን ነኝ ብሎ የሚናገር ፤ የሚጽፍ ፤ አንድም ግለሰብ አጋጥሞኝ አያውቅም ከአንድና ከብቸኛው ዶ/ር ነገደ በቀር ፤ ጋሻ ተብሎ የሚጠራውም ሆነ ሌሎቹ ጭራሽ እነማን እንደሆኑና ምንነታቸው ለማንም ግልጽ ያልሆኑ መሆናቸውን መናገር ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል ፤ በደፈናው ጨፍኑና እናሞኛችሁ ነው የሚሉን ፤ ግን እስከመቼ ነው መልሱ?

መቼም ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም ሲባል እንሰማ ነበር የዘንድሮዎቹ ግን ቅስናውንማ ተረከብን ተክነነዋል አሁን ጵጵስናው ይሰጠን እያሉ ሲንጫጩ መመልከት የግድ ሆኗል፤ ምናልባትም ከላይ እንደጠቀስኩት እንደ ባቢሎናውያን ቋንቋችን ተለዋውጧል አሊያም እንደ ታምራት ላይኔ አዲሱ ቤተሰቦቹ ልዩ ልሳን እየተነጋገርን እርስ በርስ መግባባቱ አቅቶናል ማለት ነው ።

ወያኔ ጠላት አይደለም ሆኖም ግን ወግተን ከስልጣን እናስወግደዋለን ፤ ወደ ፓርላማ እንድንገባና ለቀጣዩ ውድድር እንድንሰለፍ ከፈቀደልን ደግሞ የፓርላማውን ወንበር ይዞ ለመስራት ዝግጁ ነን ይላሉ ። እንዴት ነው ይሄ ይውጋሽ እያሉ ይማርሽ ማለት? በዚህ ይዘት ነው ወያኔን እናስወግዳለን እየተባለ የሚሾፍብን ? እንዴት ተቀልዱል ጎበዝ ? ነጋሪ ቢያጡ ነው እና ችላ ሊባሉ አይገባም ።

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ያሸንፋል!!